እናንተ ሰዎች ሆይ! አላህ መልካም ነው። ከመልካም በቀርም አይቀበልም። አላህ መልክተኞችን ባዘዘው ነገር አማኞችንም አዟል።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "እናንተ ሰዎች ሆይ! አላህ መልካም (ጥሩ) ነውና ከመልካም (ከጥሩ) በቀር አይቀበልም። አላህ መልክተኞችን ባዘዘው ነገር አማኞችንም አዟል። አላህ እንዲህ ብሏል: {እናንተ መልክተኞች ሆይ! ከተፈቀዱት ምግቦች ብሉ። በጎ ስራንም ስሩ። እኔ የምትሰሩትን ሁሉ አዋቂ ነኝ።} [አልሙእሚኑን:51] እንዲህም ብሏል: {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከነዚያ ከሰጠናችሁ ጣፋጮችን ብሉ።} [አልበቀራህ: 172]" ቀጥለውም ጉዞ የሚያረዝም፣ ጨብራራ፣ ፊቱንና ልብሱን አቧራ ያለበሰው አንድ ሰውዬ አወሱ። እጁን ወደ ሰማይ እየዘረጋ: "ጌታዬ ሆይ! ጌታዬ ሆይ! እያለ
ይለምናል። ምግቡ ሐራም ነው። መጠጡ ሐራም ነው። ልብሱ ሐራም ነው። በሐራም ነው የተገነባው። እንዴት ለርሱ ዱዓው ተቀባይነት ይኖረዋል?" አሉ።»
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና አላህ መልካም፣ ከጉድለትና ነውር የጠራና የፀዳ፣ በምሉዕነት የሚገለፅ መሆኑን ተናገሩ፤ ከተግባርም፣ ከንግግርና ከእምነትም መልካም የሆነውን እንጂ እንደማይቀበል ተናገሩ። እርሱም ለአላህ ጥርት ተደርጎ የተሰራና የነቢዩን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና መመሪያ የተከተለ ስራ ነው። በዚህ ካልሆነ በቀርም ወደ አላህ መቃረብ አይገባም። ለአንድ አማኝ ስራው መልካም ከሚሆንበት ትላልቅ ነገሮች መካከል ምግቡ መልካም መሆኑ ነው። ይህም የተፈቀደውን መመገቡ ነው። በዚህም ስራው ይፀዳል። ስለዚህም የተፈቀደን በመብላትና መልካም በመስራት አላህ መልክተኞችን እንዳዘዘው ሁሉ አማኞችንም አዘዘ። አላህ እንዲህ አለ: {እናንተ መልክተኞች ሆይ! ከተፈቀዱት ምግቦች ብሉ። በጎ ስራንም ስሩ። እኔ የምትሰሩትን ሁሉ አዋቂ ነኝ።} እንዲህም አለ: {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከነዚያ ከሰጠናችሁ ጣፋጮችን ብሉ።} ቀጥለው ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ምንም ያህል ተቀባይነትን የሚያስገኙ ግልፅ ሰበቦችን ቢፈፅም ስራን የሚያበላሽና ተቀባይነቱን የሚያሳጣ ከሆነው ሐራም ምግብ ከመብላት አስጠነቀቁ። ለዱዓ ተቀባይነትን ያስገኛሉ ከተባሉት ግልፅ ሰበቦች መካከልም: የመጀመሪያ: እንደ ሐጅ፣ ጂሃድ፣ ዝምድናን መቀጠልና ከዚህም ውጪ ላሉ ነገሮች ለአምልኳዊ አላማዎች ጉዞን ማርዘም ነው። ሁለተኛው: ባለማበጠር ምክንያት የፀጉሩ መበታተንና በአፈር (በአቧራ) ምክንያት የልብሱ ቀለምና የሰውነት መልኩ መለወጡ ነው። ይህም አስገዳጅ ችግር የገጠመው መሆኑ ነው። ሶስተኛው: ወደ ሰማይ ዱዓ በማድረግ እጁን ከፍ ያደርጋል። አራተኛው: ጌታዬ ሆይ! ጌታዬ ሆይ! እያለ ወደ አላህ በስሞቹ ይቃረባል፣ በዚህም ችክ ይላል። ከነዚህ ለዱዓ ተቀባይነትን ከሚያስገኙ ምክንያቶች ጋር ሆኖም ግን ዱዓው አልተሰማም። ይህም ምግቡ፣ መጠጡና ልብሱ ሐራም ስለሆነና በሐራም ስለተገነባ ነው። ባህሪው ይህ የሆነ ሰው ተቀባይነት ማግኘቱም ሩቅ ነው። አላህስ እንዴት ዱዓውን ይቀበለዋል?

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/4316